# ስለ ሥራ ፈላጊዎችና ስለ ክፍት ሥራ ቦታዎች አመዘጋገብ ሥነ ሥርዓት የወጣ መመሪያ



Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

# ስለ ሥራ ፈላጊዎችና ስለ ክፍት ሥራ ቦታዎች አመዘጋገብ ሥነ ሥርዓት የወጣ መመሪያ

## 1. አውጭው ባለሥልጣን

በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 42/1985 አንቀጽ 170/1/በ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሠራተኛና ማኀበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ስለሥራ ፈላጊዎችና ስለክፍት ሥራ ቦታዎች አመዘጋገብ ሥነ ሥርዓት መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ

1. "ለማጅ" ማለት በድርጅት ውስጥ በተለየ ሙያ እየሠለጠነ ለድርጅቱ አገልግሎት ለመስጠት ገዴታ የሚገባ ሰው ነው፡፡
2. "አሠሪ" በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 42/1985 አንቀጽ 2/1/ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡
3. "ሥራ ፈላጊ" ማለት ማናቸውም የመሥራት ፈላጎትና ችግሎታ ያለው ዕድሜው አሥራ አራት እና ከዚያ በላይ የሆነና በሕግ ከተወሰነው የጡረታ ዕድሜ ያልደረሰ ሰው ነው፡፡
4. "ጽ/ቤት" ማለት የክልል መስተዳድር ወይም የዞን ወይም የወረዳ ሠራተኛና ማኀበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ነው፡፡
5. "ድርጅት" በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 42/1985 አንቀጽ 2/2/ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

## 4. ስለ ሥራ ፈላጊዎች አመዘጋገብ

1. ማንኛውም ሥራ ፈላጊ የሚከተሉትን መረጃዎች በግንባር ማቅረብ በሚኖርበት አድራሻ ባለው ጽ/ቤት ሊመዘገብ ይችላል፡፡

   ሀ/ የራሱን መታወቂያ፣



Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ለ/ የሥራ አጥ ወይም በሥራ ላይ የቆዩና ያቋረጠ ወይም በሥራ ላይ መሆኑን ማረጋገጫ፣

ሐ/ የትምህርት የሙያና የሥራ ልምድ የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣

መ/የዕድሜ ማስረጃ፣

ሠ/ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች፣

2. ሥራ ፈላጊው ከምዝገባ በኂላ የሙያ ወይም የትምህርት ማሻሻል ካደረገ ይህንኑ ያስመዘግባል፡፡

## 5. ስለ ምዝገባ ማረጋገጫ ካርድ

1. ሥራ ፈላጊው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4/1/ የተመለከቱትን ማስረጃዎች ካሟላ በዚሁ በተዘጋጀው ቅጽ ወይም ባህር መዝገብ በቅደም ተከተል ተመዝግቦ የምዝገባ ማረጋገጫ ካርድ ይሰጠዋል፡፡

2. ሥራ ፈላጊው የተሰጠው የምዝገባ ማረጋገጫ ካርድ ከጠፋበት ሁኔታውን በፖሊሲ ጣቢያ በማስመዝገብ አዲስ የምዝገባ ማረጋገጫ ካርድ ሊያወጣ ይችላል፡፡

3. የምዝገባ ማረጋገጫ ካርድ ሲቀደድ ወይም ሲላጥ ወይም በአጠቃላይ ሲበላሽ፣ ሥራ ፈላጊው ይህንኑ በማስረዳት ካርዱ እንዲታደስለት ሲጠይቅ በቀድሞው የምዝገባ ቅደም ተከተል መሠረት አዲስ የምዝገባ ማረጋገጫ ካርድ ይሰጠዋል፡፡

4. ማንኛውም ሥራ ፈላጊ የተመዘገበበትን ካርድ ሰርዞና ደልዞ ወይም በማጭበርበር ተመዝግቦ ቢገኝ የምዝገባ ካርዱ ይሰረዝበታል፡፡ ይህም እርምጃ ሥራ ፈላጊውን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4/1/ የተመለከቱትን ማስረጃዎች በማሟላት አዲስ የምዝገባ ማረጋገጫ ካርድ ከማውጣት የሚያግደው አይሆንም፡፡

5. ሥራ ፈላጊ ከጽ/ቤቱ ለሚሰጠው የምዝገባ ማረጋገጫ ካርድ ምንም ዓይነት ክፍያ አይጠየቅም፡፡

## 6. የምዝገባ ማረጋገጫ ካርድ ስለሚይዛቸው ነገሮች

የምዝገባ ማረጋገጫ ካርድ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትንና አግባብ ያላቸውን ሌሎች መግለጫዎች ይይዛል፡፡



Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ሀ/ የሥራ ፈላጊውን

- ሙሉ ስም ከአያት ስም ጭምር
- አድራሻ /ክልል፣ዞን፣ወረዳ፣ቀበሌ፣የቤት ቁጥር/
- የቀበሌ መታወቂያ ቁጥር

ለ/ ምዝገባ የተፈጸመበት ቀን
ሐ/ የሙያ መደብ ቁጥር
መ/ የመዝጋቢው ሙሉ ስም፣ፊርማ

## 7. ስለክፍት የሥራ ቦታዎች አመዘጋገብ

ክፍት የሥራ ቦታ ከአሠሪ ሲገለጽ ለዚሁ በተዘጋጀው ቅጽ ላይ ይመዘገባል፤ ቅጹም ከዚህ በታች የተመለከቱትንና እንደ አስፈላጊነቱም ሌሎችንም መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፡፡

ሀ/ የአሠሪውን ስም፣ አድራሻና የሚያካሄደው የሥራ ዓይነት፣
ለ/ የክፍት የሥራ ዓይነት፣ ብዛት፣ ደረጃና ደመወዝ፣
ሐ/ የሚፈለገው ሙያ፣ ትምህርትና የሥራ ልምድ፣
መ/ የቅጥሩን ሁኔታ፣
ሠ/ ክፍት የሥራ ቦታው የተፈጠረበትን ምክንያት፣

## 8. ስለክፍት የሥራ ቦታዎች ማስታወቂያ

1. ከአሠሪ ክፍት የሥራ ቦታ መኖሩ የተገለጸለት ጽ/ቤት መረጃው በደረሰው በ5 ቀናት ውስጥ ይህንኑ ለዚሁ በተዘጋጀው የማስታወቂያ ሰሌዳዎች ላይ ያወጣል፣

2. ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያው ሥራው የሚጠይቀውን ትክክለኛ ችሎታ የተወዳዳሪዎቹ ምዝገባ የሚካሄድበትን ቦታ ቀንና ሰዓት እንዲሁም ለውድድሩ የሚፈለጉትን ማስረጃዎች በግልጽ የሚያመለክት መሆን አለበት፣

3. ማንኛውም ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ ከውድድሩ በፊት ቢያንስ ለ3 ተከታታይ ቀናት ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ የክፍት የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ እንዲቆይ መደረግ አለበት፣

4. በወጣው ማስታወቂያ መሠረት ተወዳዳሪ ካልቀረበ ለአንድ ጊዜ ብቻ ለ2 ተከታታይ ቀናት የሚቆይ ድጋሜ ማስታወቂያ እንዲወጣ ይደረጋል፣



www.chilot.me

Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

5. ድጋሚ ማስታወቂያ ወጥቶ ተወዳዳሪ ካልቀረበ ማስታወቂያ በወጣ በ3 ቀናት ውስጥ ሁኔታው ለጠያቂው አሠሪ ይገለጻል፣

## 9. <u>መራጭ ቡድንን ስለማቋቋምና ሥራ ፈላጊዎችን ስለመምረጥ</u>

1. በአሠሪዎች ለሚገለጹ ክፍት የሥራ ቦታዎች ሥራ ፈላጊዎችን የሚመርጥ መራጭ ቡድን እንደአስፈላጊነቱ በጽ/ቤቱ ውስጥ ማቋቋም ይቻላል፣

2. ለተገኘ ክፍት የሥራ ቦታ የሚደረገው ምርጫ ከተመዘገቡና ከቀረቡ ሥራ ፈላጊዎች መካከል ብቻ ሲሆን፣ ምርጫው ለሥራው የተጠየቀውን መመዘኛ መሠረት በማድረግ መካሄድ ይኖርበታል፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ሥራ ፈላጊዎች እኩል ወይም ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ ሲኖራቸው የትምህርት ውጤታቸውና የምዝገባቸው ቅደም ተከተል የመመረጥ ቅድሚያን ያስጣሉ፣

4. የተመዘገቡ ሥራ ፈለጊዎች ለክፍት የሥራ ቦታው የተጠየቀውን መመዘኛ የማያሟሉ ሆኖ ሲገኝ ይኸው በታወቀ በ10 ቀናት ውስጥ ለጠያቂው አሠሪ ሁኔታው ይገለጻል፣

5. ለተጠያቂው አሠሪ ለመላክ ለአንድ ክፍት የሥራ ቦታ የሚመረጡ እጩዎች ከሰባት ያላነሱ ከአሥር ያልበለጡ ይሆናሉ። ሆኖም የቀረቡት ሥራ ፈላጊዎች ከሰባት ካነሱ እነዚሁ ይላካሉ፣

6. የተመረጡ ሥራ ፈላጊዎች ወደጠያቂው አሠሪ ሲላኩ ከላኪው ጽ/ቤት የማገናኛ ካርድ ወይም ደብዳቤ ይሰጣቸዋል፣

## 10. <u>ሥራና ሠራተኛን አገናኝ ስለማገናኘት</u>

1. ሥራና ሠራተኛን የሚያገናኝ ጽ/ቤት ለዚሁ ዓላማ፣

   ሀ/ ከአሠሪ ጋር በሚኖረው ግንኙነት መሠረት ስለሚፈጠር ክፍት የሥራ ቦታዎች መረጃ ይሰበስባል፣ ክፍት የሥራ ቦታዎቹም በወቅቱ እንዲገለጹለት አሠሪዎቹን ያበረታታል፣



Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

ለ/ በዚህ መመሪያ መሠረት ሥራ ፈላጊዎችንና ክፍት የሥራ ቦታዎችን ይመዘገባል፣ የክፍት ሥራ ቦታ ማስታወቂያ ሠሌዳዎችን እንደአስፈላጊነቱ አመቺ በሆነ ሥራፍራዎች በማቋቋም የተመዘገቡ ክፍት የሥራ ቦታዎች በሚጠይቁት መመዘኛዎች መሠረት ለሥራ ፈላጊዎች ማስታወቂያ ያወጣል። በማስታወቂያ ለወጣውም ክፍት የሥራ ቦታ የሚመጥኑ ሥራ ፈላጊዎችን መልምሎ ለአሠሪ ይልካል፣

ሐ/ በጥያቄው መሠረት ለአሠሪ የተላኩ ሥራ ፈላጊዎች መቀጠራቸውን ወይም አለመቀጠራቸውን ይከታተላል፣

መ/ የሥራ ፈላጊዎችንና የክፍት የሥራ ቦታዎችን የምዝገባ ሪከርድ ይይዛል፣ ስታትስቲክስ ያዘጋጃል፣ ይህንም ለሚመለከተው ያሰራጫል፣

ሠ/ በዚሁ መመሪያ መሠረት እንደ ሁኔታው አሠሪ ለማጆችን በተለየ ሙያ ለማሰልጠን ጥያቄ ሲያቀርብ መልምሎ ይልካል፣

## 11. ማስረጃዎችን ስለማቅረብ

ማንኛውም አሠሪ በዚህ መመሪያ መሠረት ሥራ ፈላጊን የላከለት ጽ/ቤት የሚጠይቀውን ተገቢ መረጃ ማቅረብ አለበት።

## 12. መመሪያው ስለሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከግንቦት 15 ቀን 1987 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት 15 ቀን 1987 ዓ.ም.

መንበረ ዓለማየሁ

የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር


Created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional